የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሠባተኛ ዓመት ቁጥር 24
ሠመራ ሠኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺፯

በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ምክር-ቤት
ጠባቂነት የወጣ

7th year No 24
Samara- 7th July, 2004

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር **15/94** ዓ.ም የክልል አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለማስወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር .....ገጽ **1**

አዋጅ ቁጥር **24/1996**

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የክልል አስፈፃሚ አካላት አዲስ አደረጃጀት ሴክተር ቢሮዎችን ለማጠፍና ተመሳሳይ የስራ ተግባራት ያላቸውን አካላት ውጤት እንዲታይ በማስፈለጉ፣

በአፋር በሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተሻሽሎ በወጣው ህገ-መንግስት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል (ሀ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 24 /96 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

<u>አንቀጽ ሁለት</u>

ከዚህ አዋጅ የሚከተሉት ተሻሽለዋል

1. አንቀጽ አራት ንዑስ አንቀጽ 12

ሀ/ #የውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ሃብት ጽ/ቤት; በሚል ተተክቷል።

ለ/ #የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ; ራሱን በመቻል ቢሮ በመሆን ይቀጥላል።

2. አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) #የንግድ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ኢንቨስትመንት ቢሮ; ይል ነበር# ንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርት ኢንቨስትመንት ቢሮ; በሚል ተተክቷል።
   አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 3 በፊደል (ሐ) የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት የሚል ተሰርዞ አንቀጽ 2 በተጠቀሰው ቢሮ ስር ተጠቃሏል።
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ ቁጥር #2 ፊደል #ሐ; #የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ; ተብሎ ሲጠራ የነበረው ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን; በሚል ስያሜ ተተክቷል።
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ ቁጥር 4

(ሀ) የሥነ ህዝብ ጽ/ቤት;

(ለ) የገቢዎች ጽ/ቤት; ተብሎ የተቋቋመው ተሰርዞ# በፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ማስተባበሪያ ; ስር እንዲደራጅ ተደርጓል።

5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ፊደል (ሰ) የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ነበረው ታጠፎ# እንስሳትና አካባቢ ጥበቃ ቢሮ; ስር ተካትቶ በዚህ ቢሮ በመምሪያ ደረጃ እንዲዋቀር ተደርጓ።
6. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ቁጥር 6 ፊደል (ለ) ሠራተኛናማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ፊደል (መ) የህዝብ ተሳትፎ አደረጃጀት ጽ/ቤት ፊደል (ሠ) የሰፈራ ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የተጠቀሰው ቢሮና ጽ/ቤቶች ታጥፈው በማስታወቂያና የህዝብ አደረጃጀት ጉዳይ ማስተባበሪያ ቢሮ ስር እንዲታቀፉ ተደርጓል።
7. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 36 የድንበር ጉዳይ ተብሎ የተጠቀሰው ቃል ተሰርዞ የወሰን ጉዳይ ጽ/ቤት ተብሏ ተተክቷል።
8. በዚህ አዋጅ ቁጥር አንቀጽ ቁጥር 41 ንዑስ አንቀጽ 1 የተቋቋሙት አከላት በክልሉ ውስጥ እንደአስፈላጊነቱ በዞን በወረዳ ወይም በሁሉም እርከኖች ቅርንጫፍ መ/ቤቶች ሊኖራቸው ይችላል። የተባለው ተሸሮ በተጠቀሰው አንቀጽና ቁጥር መሰረት በወረዳ ደረጃ ቅርንጫፎች ሊኖራቸው የሚችል ሲሆን በዞን ደረጃ ግን የዞን አስተዳደርና የፍትህ አካላት ይኖራሉ። ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብና መመሪያ ይወሰናል።

አንቀጽ ሶስት

የታጠፉ ቢሮዎችን ጽ/ቤቶች ስልጣንና ተግባር ማስተላለፍ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩ ጽ/ቤቶችና ቢሮዎች አዋጅ ቁጥር 15/1994 ተሰጥቷቸው የነበረው ሥልጣን እና ተግባር ወደ ታጠፈበት ቢሮ ተሸጋግሯል።

አንቀጽ አራት

የተሻሩ ህጎች

1. **በዚህ አዋጅ አንቀጽ ሁለት የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ተሰርዞ በንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ስር የተጠቃለለ በመሆኑ የተሻሻለው የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 23/96 በዚህ አዋጅ ተሸሯል።**
2. **የክልሉን ንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኢንቨስትመንትን እንቅስቃሴ ተግባር የሚወሰን ደንብ ማውጣት ይችላል።**

አንቀጽ አምስት

መሸጋገሪያ

የታጠፉ ቢሮዎች ይሰሯቸው የነበሩ ስራዎችና ጥቅሞቻቸው በሙሉ ወደ ታጠፉበት ቢሮ ገብተው ተፈፃሚ ይሆናሉ።

ሰኔ--------- 1996 ዓ.ም ሠመራ

እስማኤል አሊ ሴሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር